የደቀ መዝሙርነት መርሐዎች

የክርስትና ሕይወት መርሐዎች

የጥናት መመሪያ

የክርስቲያን ሥነ-ምግባሮች

ትምሕርት 3፥ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት:- ክፍል 2

መግቢያ

ይህ ትምሕርት ከደቀመዝሙርነት መርሐዎች የትምሕርት መድብሎች አንዱ አካል ሲሆን፣ ርዕሱም “የክርስቲያን ሥነ-ምግባሮች” ይባላል። ይህ ተከታታይ ትምሕርቶችን ያቀፈው ክፍል፣ የክርስቲያን ሕይወት ሥነ-ምግባሮችን ማለትም:- ፀሎት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ እንደዚሁም አእምሮአችንን ዘላለማዊ ነገሮች ላይ ማሳረፍን ጨምሮ ያስተዋዉቃል። ይህ አስደናቂና አስደሳች ይዘት ወይም ፅንሰ ሃሳብ፤ ለነባርና በሳል አማኞች መንፈሳዊ ሕይወት ጉልበትና ጥንካሬ መስጠት አለበት፤ እንዲሁም ደግሞ፥ አዳዲስ አማኞችን ወደ ጠለቀ እምነት ማራመድ፥ማፍጠን ይገባዋል። ይህ በአፈፃፀም ባሕርይዉ ተግባራዊ የሆነዉ ጠቃሚ የትምሕርት መርጃ (ማቴሪያል)፥ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት ወደፊት ሊቀበል ያለዉ ብዙ መንፈሳዊ ዋጋ ወይም ወረታዎች ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋል።

የጥናት መመሪያዉ ዓላማ ግለሰቦች የተለያዩ ትምሕርቶችን እያንዳንዳቸዉን በተናጠል ወስደዉ በጥልቀት እንዲመረምሩና በግላቸዉ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለመርዳት ነዉ። ይህ ትምሕርት ከሌሎች “የደቀመዝሙርነት መርሐዎች” ማቴሪያሎች፥ ማለትም፥ ጽሁፎች፥ ኦዲዮ፥እና ቪዲዮ ዉጤቶች ጋራ በጥምረት መጠቀም ይቻላል።
በድረ፡ገፃችን፥ www.DEamharic.org ይመልከቱ።

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድቶ የታተመ ነዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.

የክርስቲያን ሥነ-ምግባሮች
ትምሕርት 3፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፡- ክፍል 2

የትምሕርቱ ትኩረት?

ይህ ትምሕርት፣ የጀመርነዉን የኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመቀጠል፤ ከኢንተርፕሪቴሽን እና፣ አፕሊኬሽን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃዎች ወይም አካላት ጋራ ያስተዋዉቀሃል።

ፈጣን ግንዛቤ...

ይህ ትምሕርት ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን መመልከት ይቀጥላል። በዚህ ትምሕርት ዉስጥ፣ የኢንተርፕሪቴሽን እና፣ የአፕሊኬሽን ደረጃዎችን አተገባበር ትለማመዳለህ። በዚህ ትምሕርት ዉስጥ፣ የኢንተርፕሪቴሽን እና፣ የአፕሊኬሽን ሃሳብህን ለመደገፍ ሁል ጊዜም በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መመሥረት በጣም አስፈላጊ ነዉ። የራሳችን አእምሮ አንዳንድ ጊዜ ባልሆነ አካሄድ ሊያሳስተንና ካልሆነ ማጠቃለያ ላይ ያስዘልለናል፤ የምንረዳዉም መጽሐፍ ቅዱስ የማይናገረንን ሊሆን ይችላልና ታላቅ ጥንቃቄ ይጠበቅብናል። ፀሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ ዋነኛዉ አካል ነዉና አፅንተህ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገር። ቃሉን እንድንረዳ እግዚአብሔርን መጠየቅ የምንችለዉ፤ እርሱም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚፈፅምልን በብርቱ ፀሎታችን ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ አንዴ እዉነትን ተረድተን ከጨበጥን፣ እነዚያን እዉነቶችና መንፈሳዊ ነገሮች ተግተን በተግባር ላይ ማዋል ይገባናል። መጽሐፍ ቅዱስህን የምታነብበትን መንገድ፣ ወደተሻለ ደረጃ ለመለወጥ ዝግጁ ነህን?

እንጀምር

1. **አብዛኛዉን ጊዜ የትኛዉን ጥቅስ ነዉ ለማጥናት የላቀ ፍላጎት ያለህ? የትኛዉንስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነዉ አዘዉትረህ ለመመልከት የምትነሳሳዉ?**

2. **መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ወይም ፍች (ኢንተርፕሪቴሽን) የሚያስፈልገዉ ለምንድን ነዉ? መጽሐፍ ቅዱስ ጠንከር ያለ ሥራ ካልታከለበት፤ እንዲያዉ እንደዋዛ በአንድ እይታ የማይገባ፤ ለመረዳትም ቀላል እንዳይሆን አስተዋፅኦ ያደረጉት ምክንያቶች ምንድን ናቸዉ? "ኢንተርፕሪቴሽን" እና፣ "አፕሊኬሽን" የሚባሉት ቃላት ትርጓሜ ምንድን ነዉ?**

ጥናት

❖**የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መፍታትን መማር፡-** የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ከተመለከትን (ካነበብን) በኋላ፣ ቁልፍ የሆኑ ዝርዝሮቹን ለማስተዋል፤ ፍች ለመስጠት ዝግጁ ነን ማለት ነዉ። አንድን ዱኩሜንት ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላኛዉ ቋንቋ የሚፈታ ወይም የሚመልስ ሰዉ ሚና ተርጓሚ ይባላል። ይህ ሥራ፣ የሁለቱንም ቋንቋዎች ታላቅ እዉቀት የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ቀጥተኛ ወይም ቃል በቃል ትርጉም፣ ዉጤታማ የግንኙነት ወይም የመልእክት ማስተላለፊያ መንገድ አይደለም። ስለዚህ፣ ተርጓሚ የቃሎቹን ትርጓሜ በሚገባ መረዳትና፤ ጽሑፉ የሚለዉን ፍች ለታለመለት ተደራሲ ወይም አንባቢ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም እና ፍችዉን ማብራራት፣ በእርግጥ ትርጓሜዉን በትክክል ማስተዋልና መጨበጥን ይጠይቃል።

➢**ፍች መስጠት ጥያቄዎች መጠየቅን ይፈልግብናል፡-**

○ይህ ጥቅስ እዚህ ክፍልና ሥፍራ መሆን ያስፈለገዉ ለምንድን ነዉ?

○ጸሐፊዉ በዚህ ጥቅስ ምን ለማለት ፈለገ?

○ይህ ጥቅስ፣ በቀደሙት ቁጥሮች ዉስጥ ከሰፈሩት ጥቅሶችና ክፍሎች፣ ብሎም ጥቅሱን ተከትለዉ ከሚመጡት ጥቅሶችና ክፍሎች ጋራ ተያያዥነት ያለዉ እንዴት ነዉ?

➢**ቁልፍ የሆኑ ቃላትን መለየት፡-** ይህ ምናልባትም በሚገባ የማታዉቃቸዉን ቃላት ትክክለኛ ትርጉም ለማግኘት፤ መዝገበ ቃላትን መጠቀም ያስፈልግህ ይሆናል። ቁልፍ ቃላት የሚባሉት፣ ለጥቅሱ መልእክት በጣም አስፈላጊ የሆኑት ናቸዉ። አንዳንድ ጊዜ፣ የተወሰኑ ቃላትን፣ በተለይም አንዱ ቃል ሲደጋገም ወይም፣ በርካታ ትርጓሜዎች ሲኖሩት በቅርበት መመርመር ያስፈልገሃል። አንዳንድ ጥያቄዎችን ራስህን ጠይቅ፣ ለምሳሌ፡- ቃሉን በዚህ መጽሐፍ በተለያዩ ሥፍራዎችና ጥቅሶች ዉስጥ እንዴት ተጠቀሙበት? በሙሉዉ መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ እንዴት ጥቅም ላይ ዋለ? እንዲሁም፣ በአለበት ሥፍራ አገባቡ የሚሰጠዉ አጠቃላይ ትርጓሜና ስሜት ምን ይመስላል? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸዉ።

➢**የምታጠናዉን ጥቅስ ለመፍታትና ለመገንዘብ እንዲረዱህ ሌሎች ጥቅሶችን በማመሳከር ተጠቀም፡-**

○በጥቅሱ አገባብ የቅርብ የሆኑት (በጥቅሱ ዙሪያ ቀድመዉና ተከትለዉ ያሉት ጥቅሶች) ምን ያመለክታሉ?

○ሰፋ ያለዉ ጽሑፍ አገባብ ምን ያመለክታል (መጽሐፉ፣ የመጽሐፉ ዓይነት፣ ወዘተ..)?

○ማጣቀሻ መረጃዎች ማለትም፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ያሉና፣ ተዛማጅ ሃሳብ ያላቸዉ ማመሳከሪያ ጥቅሶች ምን ያመለክታሉ?

➢**ማስታወሻዎችን መያዝ፡-** ከጥቅሱ መልእክት ዉስጥ ተረድተህ የተቀበልካቸዉን፣ ሥነ-ምግባሮችና፣ መሠረታዊ መርሆዎች ዝርዝር አስፍር።

➢**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማቴሪያሎችንና ግብአቶችን ግኝት ማጣራት፡-** በኢንተርኔት ድረ-ገፆች ዉስጥ ብዙ የጥናት ማቴሪያሎች ወይም ልዩ ልዩ መረጃዎች አሉ። ተማሪዎችህ የሚያመሳክሩባቸዉን ተዛማጅ ድረ-ገፆችን፤ የአብያተ ክርስቲያናት ቤተ መጽሕፍትን፤ እንዲሁም ያለችግር መጠቀም የሚችሏቸዉን መርጃ መሣሪያዎች መጠቆም፥ ማመላከት ያስፈልጋል።

➢**የደራሲዉን (የጸሐፊዉን) ፍላጎት እና መልእክት አጠቃልሎ በግልጽ ያሰፈረ፤ እጥር ምጥን ያለ መግለጫ ፃፍ።**

❖**ኢንተርፕሪቴሽን እና አፕሊኬሽን ምን ይመስላሉ?** ከዚህ በቀደመዉ ትምሕርት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ፥ ሉቃስ 19:1-10 ያለዉን ታሪክ መርምረን ነበር። አሁንም ደግሞ ከዚያዉ ክፍል የጥቂት ጥቅሶችን፡- አብዘርቬሽን፥ ኢንተርፕሪቴሽን እና፥ አፕሊኬሽን ምን ሊመስሉ እንዲሚችሉ ሠርተን እንመልከት (ከዚህ ትምሕርት በስተመጨረሻ፥ በማመሳከሪያነት የምትመለከተዉ ሙሉ ሠንጠረዥ ተያይዞልሃል)።

❖**በኢንተርፕሪቴሽን ተለማመድ፡-** አንድ ሰዉ የኢንተርፕሪቴሽንን ማለትም፥ ፍች መስጠትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃ ወይም አካል፣ በእርግጠኛነት ለመረዳት፣ ያለማመንታት በተግባር ማድረግ አለበት! መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ የተላከ የእግዚአብሔር መልዕክት እስከሆነ ድረስ፤ ብዙ የተለያዩ የአፈፃፀምና የአተገባበር መንገዶች ይኑሩት እንጂ፤ እያንዳንዱ ጥቅስ ትክክለኛ ትርጓሜ ወይም ፍች አለዉ። ስለዚህ ጥቅሱን በሚገባ ለመረዳት በትጋት ማጥናት ጠቃሚ ነዉ፤ አለበለዚያ ፍፃሜአችን (ዉጤቱ) የተሳሳተ እምነት ላይ መዉደቅ ሊሆን ይችላል።

➢ለዚህ ምሳሌ እንዲሆንህ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት፥ ፊልጵስዩስ 4:13 ን ዉሰድ። ጥቅሱ እንዲህ ይላል፡- "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።" ይህም ለማሰላሰል የሚጥም አስደሳች ጥቅስ ስለሆነ፥ አንድ ሰዉ ኢንተርፕረት ሲያደርግ ወይም ትርጓሜዉን፣ 'እኛ በሃሳባችን የመጣዉን ማንኛዉንም፡- ከሰብአዊ ባህሪ ዉጭ የሆነ፥ መለኮታዊ ድርጊት ማከናወን እንችላለን!' የሚል ፍች ሊሰጠዉ ይችላል። "ሁሉን" የሚለዉ ቃል ራሱ ምናልባትም ዘርዝረን የምንጨርሰዉ ላይሆን ይችላል፤ አይደለም እንዴ? ይሁን እንጂ፥ የጥቅሱን አዉድ በቅርበት ለማጤን፤ ከዚህ ቁጥር በፊት ያሉትን ቁጥሮች ከነሙሉ አንቀፁ ስንመለከት አገባቡ የሚያሳየን፤ 'መጥፎ ገጠመኞችን በመቋቋም፣ በማንኛዉም ሁኔታ ዉስጥ ደስ ስለመሰኘትና ስለመርካት ነዉ'። በማንኛዉም ሁኔታ ዉስጥ የመርካት ምሥጢር (ቁጥር 12) በቀጥታ እዚያ ጥቅስ ዉስጥ አልተገለጠም፤ ግን በምዕራፉ ሙሉ አካል ዉስጥ ተመልክቶአል። ፊልጵስዩስ መጽሐፍ ዉስጥ ይህ ምዕራፍ፤ ፍርሃትና ጭንቀትን አስወግዶ በምትኩ፣ ምሉዕ ደስታንና በእግዚአብሔር መታመንን ስለመምረጥ ነዉ የሚያስተምረዉ። የፊልጵስዩስ 4:13 ትክክለኛ ትርጓሜ ወይም ፍች (ኢንተርፕሪቴሽን) ሊሆን የሚችለዉ፡- "በፈተና እና መጥፎ ገጠመኝ መካከል እንኳን ሆነን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት፥ ሰላምና ደስታን ልንጎናፀፍ እንችላለን" የሚል ነዉ።

➢አሁን ደግሞ አንድ ጥቅስ ወስደን አብረን እንለማመድ። ሮሜ 12:1-2 ን አንብበህ የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች መልስ፡-

የእነዚህን ቃላት ትርጉም እንዴት ታቀርባለህ፡- አትምሰሉ፥ መታደስ፥ ርኅራኄ?	

ጳዉሎስ “ይህን ዓለም አትምሰሉ” እና “በልባችሁ መታደስ ተለወጡ” ሲል ምን ማለቱ ነዉ? ለማጣቀሻነት፡- 1ኛ ዮሐንስ 2:15-16፣ ቆላስይስ 3:1-4፣ ኤፌሶን 4:22-24 ን አንብብ	
ከጥቅሱ ነቅሰህ በማዉጣት የራስህ የምታደርጋቸዉ መርሆዎች (ፕሪንስፕልስ) ምንድን ናቸዉ?	
የሮሜ 12:1-2 አጠር ያለ ማጠቃለያ ወይም መግለጫ ምን ሊመስል ይችላል? ምጥን አድርገህ አስፍር።	

ከዚህ ጥቅስ ልናወጣ የምንችላቸዉ አንዳንድ መርሆዎች፡-

- ○ማንኛቸዉንም ድርጊቶቻችንን በመመርመር፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚከናወኑ መሆናቸዉን ልብ ማለት ይገባናል፣
- ○ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር ላይ በማተኮር፤ ሁልጊዜም ድርጊቶቻችን ሁሉ እርሱን ደስ እንደሚያሰኙ ሆኖ መመላለስ ይገባናል፣
- ○በዚህ ዓለም ዉስጥ በዙሪያችን ያሉት ሁሉ በሚያደርጓቸዉ ነገሮች መሳብና መወሰድ የለብንም፣
- ○የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁልጊዜ መፈፀም እንችል ዘንድ፤ አእምሮአችንን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያለማቋረጥ ማደስ፣
- ○ሃሳባችንን ሁሉ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይ በሚያደርጋቸዉ ነገሮች ላይ ማሳረፍ፣
- ○ሌላኛዉ የሚቻል ማጠቃለያ ደግሞ፡- የቅድስናን ሕይወት መኖራችን በእግዚአብሔር ፊት እንደ አምልኮ ይቆጠርልናል፣
- ○ስለሆነም፣ ፊታችንን ከዓለም ላይ አንስተን ወደ እግዚአብሔር ስንመልስ፣ የበለጠ አጥርተን እንመለከተዉና፤ እርሱም ለሕይወታችን ያለዉን ዓላማ ጠንቅቀን እንረዳለን።

ስለዚህ፥ ጥቅሶችን በዚህ ሁኔታ በጥንቃቄ ስንመረምር፣ ወደ ትክክለኛዉ ትርጓሜ እንደርሳለን፤ ያም ፍች ጥቅሱን ግልፅ ያደርግልናል፤ ወደ ግንዛቤም ያደርሰናል።

❖**መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመሥርቶ መተግበርን መማር (አፕሊኬሽን)**:- በዚህ በአፕሊኬሽን ደረጃ፣ የጻፍናቸዉን መርሆዎችና፤ የአስተምህሮዉን ማጠቃለያ ወስደን፥ በሕይወታችን የምንተገብርበት ሂደት ነዉ። እናም የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች እንመልሳለን:-

➢ይህ 'እዉነት' በህይወቴ ዉስጥ ተግባራዊ የሚሆነዉ እንዴት ነዉ?

➢ከዚህ 'እዉነት' የተነሳ፣ በሕይወቴ ዉስጥ ማድረግ የምወዳቸዉ ዉሱን ወይም የተለዩ ለዉጦች የትኞቹ ናቸዉ?

➢እነዚያን ለዉጦች ለማካሄድ የሚኖረኝ ዕቅድ ምንድን ነዉ?

❖**መተግበርን (አፕሊኬሽን) መለማመድ:-** ከመጽሐፍት በተመረጡ ጥቅሶች ጥናት በመነሳት፥ የተገኙ መመሪያዎች ላይ መተግበርን (አፕሊኬሽን) በምናከናዉንባቸዉ ጊዜያት ሁሉ፤ የጥናቱን ክፍል በበረታ ፀሎት በመጀመር፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ የሚጠብቅብንን መፈፀም፥ በሕይወታችን ላይ የሚያሳድረዉን ተፅእኖ አስቀድመን፥ አመዛዝነን፥ በጥንቃቄ መመልከት ይገባናል።

➢ሮሜ 12:1-2 ጥቅስ እንደገና ተመልከት። በኢንተርፕሪቴሽን (ትርጓሜ) ደረጃ ለይተን የያዝናቸዉን፤ በራሳችን ሕይወት ተግባራዊ ማድረግ የምንችላቸዉ መርሆዎች (ሥነ-ምግባሮች) ምንድን ናቸዉ?

➢ለዚህ ጥቅስ አፕሊኬሽን ወይም ተግባራዊ ክንዋኔ የሚሆኑ የተወሰኑ ሃሳቦች ይህን ይመስላሉ:-

○ወደ ሃሳቦቼ አትኩሬና አመዛዝኜ በመመልከት፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ መሆናቸዉን ማረጋገጥ።

○ማንኛቸዉንም ድርጊቶቼን በመመርመር፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚከናወኑ መሆናቸዉን ልብ ማለት ይገባኛል።

○በምላሳችን ዉስጥ ሞትና ሕይወት ስላሉ፣ የምናገራቸዉን ሁሉ በጥንቃቄ ማድረግ ይገባኛል።

○ዕቅዶቻችንና ዉሳኔዎቻችን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እና በእርሱ ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል።

ማጠቃለያ

- ከኦብዘርቬሽን፣ ማለትም የጥቅሱን ይዘት ተንትኖ ከማስተዋል ሂደት ተከትሎ፤ ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፡- ለጥቅሱ መልእክት ፍች መስጠት(ኢንተርፕሪቴሽን) እና፣ ከጥቅሱ ፍች የተገኘዉን መርህ በሕይወት ላይ መተግበር (አፕሊኬሽን) ደረጃዎችን ሂደት ያሳትፋል።
- የመጽሕፍ ቅዱስ ኢንተርፕሪቴሽን ማለት፣ ለጥቅስ ትርጓሜ መስጠት፣ የጥቅሱ ይዘት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅን፣ ወይም ትርጉሙን ፈልጎ ማግኘትን ይጠይቃል።
- ኢንተርፕሪቴሽን በክፍሉ ዉስጥ ያገኘናቸዉን ቁልፍ ቃላት መመርመርን፤ ተያያዥ የሆኑ ወይም ተመሳሳይ መልእክት የሚናገሩትን ጥቅሶች ከሌሎች መጽሐፍት ወይም ጥቅሶች ማንበብን፤ ማስታወሻዎችን መፃፍን፤ ከጥናት መርጃ ማቴሪያሎች (መሣሪያዎች) ጋራ ማመሳከርን፤ እንዲሁም ለመልእክቱ አጭር መግለጫ ፅፎ ማጠቃለያ ማቅረብን ይጠይቃል።
- ለአንድ የጥናት ክፍል ወይም ጥቅስ፣ ተግባራዊ ክንዋኔ ስናዘጋጅ፣ ሕይወትችንን በመለወጥ ደረጃ ምን ያህል ትጋትና መሰጠትን እንደሚጠብቅብን አስቀድመን ማጤን ይኖርብናል።
- ኢንተርፕሪቴሽንን እና አፕሊኬሽንን በምናከናዉንበት ጊዜ ሁሉ፤ ወደ ተሳሳተ ማጠቃለያ እንዳንወድቅ፤ አስቀድመን ከእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛ ግንዛቤና መረዳት መጀመር ይገባናል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል፣ የእኛንም ሕይወት ያበለፅጋል።

ነፀብራቅ ጥያቄዎች

1. ጌታ መንፈስ ቅዱስ እና ፀሎት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ዉስጥ የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነዉ?

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዉስጥ ኢንተርፕሪቴሽን እና አፕሊኬሽን አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነዉ? የጥቅሱ ጽሑፍ የሚለዉን መልእክት ብቻ መገምገምና ማስተዋል (አፕሊኬሽን) ብቻ ለምን በቂ አይሆንም?

ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፡-

ሉቃስ 19:1-10

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች	ይዘቱን ማስተዋል/ አብዘርቬሽን	ትርጉሙን መፍታት/ ኢንተርፕሪቴሽን	በሕይወትህ መተግበር/ አፕሊኬሽን
1.ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮም ገብቶ ያልፍ ነበር።	ጌታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ስላቀደ (ዝቅ ብሎ ቁጥር 28 ላይ ተጠቅሶአል) ቶሎ መሄድ ይፈልግ ነበር።	ኢየሱስ ወደ መስቀሉ ያመራ ነበረ፣ ነገር ግን እርሱን ለፈለገች አንዲት ነፍስ፥ ለአንድ ሰዉ ቆም ለማለትና ለማነጋገር ጊዜዉን ሰጠ።	በአገልግሎቴና በሥራዬ ብቻ በመዋጥ፥ ወደ ሥራዬ ሳመራ፥ ቆም በማለት የእግዚአብሔርን ፍቅር ለነፍሳት ለማካፈል ያልቻልኩባቸዉን ጊዜያት በመፀፀት ዓይኖቼን ከፍቼ ለመመስከር ያነሳሳኛል።
2. እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው፥ እርሱም የቀራጮች አለቃ ነበረ፥ ባለ ጠጋም ነበረ።	ዘኬዎስ በዓለም መንግሥት ሥርዓት ዉስጥ፥ ግብር ሰብሳቢ ነበረ፣ ኃብትም አከማችቶ ነበር።	ግብር ሰብሳቢዎች፥ ከራሳቸዉ ከእሥራኤላዉያን ዜጎች ግብር ሰብስበዉ፥ ለሮማዉያኑ ገዢ መንግሥት ያስረክቡ ነበር	ሕዝቡም ግብር ሰብሳቢዎችን፥ ለጠላት የሚሠሩ አድርጎ ያያቸዉ ነበር።
3. ኢየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ስለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው።	ዘኬዎስም ኢየሱስ እዚያ እንደሆነ አወቀ። በሥፍራዉም ብዙ ሕዝብ ነበረ። ከተሰበሰበዉ ሕዝብ ሁሉ አጭር ነበረ።	በምንም ምክንያት ይሁን፥ በየትኛዉም መንገድ፣ ይህ ኃብታም ሰዉ ኢየሱስን ለማግኘት ፈለገ።	ኃብታም ሰዎች ኢየሱስን አይፈልጉም፤ ወይም ኢየሱስ አያስፈልጋቸዉም የሚለዉን ትልቅ ዉሸት አትመን።
4. በዚያችም መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ።	ከልቡ ኢየሱስን ለማየት ፈለገ። አርቆም ብልኃትን አቀደ።	የዘኬዎስ ልብ በኢየሱስ ተማርኮአል። የክርስቶስ ስብእና እና ማንነት ማራኪ ነዉና።	በእዉነት ከእግዚአብሔር ጋራ ለመገናኘት፤ አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ወይም ከሕዝብ ለየት ማለት ግድ ይሆናል።
5. ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ፥ አሻቅቦ አየና፡- “ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው።”	ኢየሱስ ዘኬዎስን ያዉቀዋል። ኢየሱስ ወደ ዘኬዎስ ቤት ራሱን ጋበዘ። ዘኬዎስንም አዘዘዉ። ኢየሱስ፥ ብልፅግናዉ ለዘኬዎስ ባስሰጠዉ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አልተመራም።	ጌታ ኢየሱስ፥ ሰዎች በሚመለከቱበትና በሚፈርጁበት ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ሰዎችን አያስወግድም ወይም አያገልላቸዉም። ሰዎች የኢየሱስ ትኩረት አይገባዉም ብለዉ የፈረጁትን ሰዉ ኢየሱስ ፈለገዉ አቀረበዉም። ይህ ክፍል፥ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ላይ ከተመለከተዉ የስማሪያዋ ሴት ታሪክ ጋር የተዛመደ ነዉ።	ማኅበረሰብ ሰዎችን የሚያይበትን ሳይሆን፤ ሁልጊዜ፥ ጌታ ኢየሱስ እያንዳንዳችንን የሚያይበትን ሁኔታና የፍቅር ዓይኖች ልብ ብለን ማስተዋል ይገባናል።

6. ፈጥኖም ወረደ በደስታም ተቀበለው።	ዘኬዎስ ቤቱን ከፍቶ ኢየሱስን ተቀበለዉ። ምላሽም ሲሰጠዉ ኢየሱስን ከእርሱ የላቀና የበላይ አድርጎ ነበር። ኢየሱስንም በቤቱ በማስተናገዱ እጅግ ተደሰተ።	ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ሰዉ ጋር በመነጋገር ብቻ አላበቃም፤ ከእርሱም ጋር በላ። ከዘኬዎስም ጋር ግንኙነትና ጎብረት ለመፍጠር ፈለገ።	ሰዎችን ከምትሰብካቸዉ ይበልጥ (ወይም በተጨማሪ) ፣ በመልካም ግንኙነት ይደሰታሉ፥ ይጠቀማሉም።
7. ሁሉም አይተው፦ “ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ” ብለው አንጐራጐሩ።	ኢየሱስ ይህን በሰዎች ሁሉ ፊት አደረገ። ኢየሱስ በዘኬዎስ አላፈረም። ሰዎች ዘኬዎስን ኃጢአተኛ ብለዉ ይጠሩታል። የእነርሱ አመለካከት ከኢየሱስ አመለካከት የተለየ ነዉ።	አሕዛብ፥ ኢየሱስ ዘኬዎስ ቤት መሄድ አልነበረበትም የሚል እምነት አላቸዉ። ራሳቸዉን ከዘኬዎስ የተሻሉ አድርገዉ ያስቡ ነበርና፤ ኃጢአተኞች ነን አይሉም። ኢየሱስ የሚጓዘዉ ኃጢአተኞችን ለመርዳትና ለማዳን ነዉ።	ከሌሎች ላቅ ያልኩ ቅዱስ ነኝ የሚል ስሜት አድሮብኛል ወይስ፤ ሰዉ በመሆኔ እንደማንኛዉም ሰዉ ኃጢአተኛነቴን ተገንዝቤአለሁ?
8. ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታን፦ “ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኵሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ” አለው።	ዘኬዎስ ተነስቶ ቆመ። ኢየሱስን ጌታ አለዉ። ወደ አደረገዉ ዉሳኔ እንዲያተኩር አመለከተዉ። ካለዉ ሁሉ እኩሌታዉ እጅግ ብዙ ገንዘብ መሆን አለበት። በመሠረቱ ንስሐ፥ የአመለካከት እና የድርጊት ለዉጥን ይጠይቃል። እዉነተኛ ንስሐ ወደ ተገቢዉ ሥፍራ፥ ወደ ኢየሱስ መመለስን ያስከትላል።	ተነስቶ መቆም የማክበር ምልክት ነዉ። ሰዎችን ባታለለበት፥ አራት እጥፍ መልሶ ለመክፈል አረጋገጠ። ለምድነዉ ይህን ያደረገዉ? የሠራቸዉን ክፉ ነገሮች በደግነት ለመካስ ፈለገ። ሉቃስ 3:8 ን ተመልከት “እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ" ይለናል።	በእርግጥ፥ ከልብ በእዉነት ንስሐ ከገባሁ፥ በሕይወቴ ለዉጥን አያለሁ።
9. ኢየሱስም፦ እርሱ ደግሞ	ኢየሱስ ዘኬዎስን “እርሱ” ብሎ በስሙ ነዉ ያናገረዉ፤ በደፈናዉ “አንተ” ብሎ አይደለም።	ኢየሱስ በነዚያ በነበሩት ሁሉ ፊት፥ የዘኬዎስን ምሕረትና መዳን ገለፀ (አወጀ)	
“..የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፤”	ያቺ ዕለት ለዘኬዎስ የመዳን ቀን ሆነችለት። ድነት የመጣዉ መቼ ነበር? በዚያዉ ኢየሱስ በመጣባት ዕለትና ቅፅበት። ዘኬዎስ በቀጥታ የአብርሃም ልጅ አልነበረም።	ኢየሱስ ድነትን ያመጣል። ዘኬዎስ በእምነቱ አማካይነት የአብርሃም ልጅ ሆኖ ተቆጠረ። (ገላትያ 3:9) ን ተመልከት።	ሰዎች እንዲድኑ በምመሰክርላቸዉ ጊዜ ሁሉ፥ ስለ ኢየሱስ መናገር እፈልጋለሁ።
10. የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።	የሰዉ ልጅ የተሰኘዉ ኢየሱስ ነዉ። ይህ የኢየሱስ መጠሪያ ነዉ፥ የተልዕኮ ደረጃዉ ነዉ፥ ሚናዉም ነዉ።	“ሊፈልግና ሊያድን” የሚለዉ፥ የዚህን ሃሳብ ማጠቃለያ ለማመልከት የገባ ነዉ።	ኢየሱስ የመጣዉ ለጠፉት ነዉ።